Treatment for Latent TB Infection Amharic

ሚኔሶታ፡ የጤና፡ ክፍል፡ ትክክለኛ፡ መረጃ (Minnesota Department of Health)


# የድብቅ ነቀርሳ በሽታ ሕክምና

የተደረገልዎት ምርመራ ድብቅ ነቀርሳ ወይም "LTBI" እንዳለብዎት ያሳያል። ጥቂት የነቀርሳ ጀርሞች በብዙ የሰዉነትዎ ክፍሎች ተሰራጭተዋል (ለምሳሌ በሳምባ፣ አጥንት ወይም በኩላሊት)።

የነቀርሳ ጀርሞቹ አሁን እየጎድዎት አይደሉም። በአሁኑ ጊዜ ጀርሞቹ "ተኝተዋል" ሆኖም ሕይወት አላቸው። ሰዉነትዎ መከላከል እስከቻለ ድረስ እነዚህ ጀርሞች እንደተኙ ይቆያሉ። ድብቅ ነቀርሳ ሲኖርዎት ለሌላ ሰዉ ነቀርሳ ሊያጋቡ አይችሉም።

ሰዉነትዎ መከላከል ሲያቆም የነቀርሳ ጀርሞቹ ይነቁና ማደግ ይጀምራሉ። **ይህ ማንም ድብቅ ነቀርሳ ያለበት ሰዉ ላይ ሊደርስ የሚችል ነው።** ጀርሞቹ አድገዉ መሰራጨት ሲጀምሩ ንቁ ነቀርሳ በሽታ ተፈጠረ ማለት ነው። ንቁ ነቀርሳ በሽታ ያላቸዉ ሰዎች በጣም ሊታመሙና ለሌሎች ሰዎች ነቀርሳ ሊያጋቡ ይችላሉ።

**የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ለመከላከል ምን ማድረግ እችላለሁ?**




ንቁ ነቀርሳ በሽታ እንዳይዘዎት ለመከላከል መዉሰድ የሚችሉት መድሃኒቶች አሉ። አይሰናየዝድ (Isoniazid ወይም INH) ለ ድብቅ ነቀርሳ ማከሚያ የተለመደ መድሃኒት ነው። INH "የተኙትን" የነቀርሳ ጀርሞች ከመታመምዎ በፊት ይገላቸዋል። የነቀርሳ ጀርሞቹም ሃይለኛ ስለሆኑ መድሃኒቱ እስከሚገላቸዉ ብዙ ወራት ይፈጃል።

INH በደንብ የሚሰራዉ ዶክተርዎ ማቆም ይችላሉ እስከሚልዎት ድረስ በየቀኑ ሲወስዱት ነው። የ INH መድሃኒትዎን ያለ ምግብ ይዉሰዱት።

ሕክምናዎ በደንብ እየተካሄደ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የINH መድሃኒት በሚወስዱበት ጊዜ ዶክተርዎ ጋር በወር አንድ ጊዜ መሄድ አለብዎት።

**ሕመም ካልተሰማኝ ለምንድነው መድሃኒት መዉሰድ ያለብኝ?**

INH የነቀርሳ ጀርሞችን የሚገድለዉ ነቅተዉ ከማሳመማቸዉ በፊት ነው። የነቀርሳ ጀርሞች እንቅልፍ ላይ እንዳሉ ለመግደል እንደሚቀል ያስታዉሱ።

**ስለ ድብቅ ነቀርሳ መድሃኒት ምን ማወቅ አለብኝ?**

ብዙ ሰዎች ያለ ምንም ችግር በየቀኑ INH ይወስዳሉ፣ ሆኖም **የሚከተሉትን ነገሮች መከታተል ይኖርብዎታል፦**

- ከሦስት ቀን በላይ የሚቆይ ትኩሳት
- የምግብ ፍላጎት አነስተኛ ሲሆን፣ የሰዉነት ክብደት ሲቀንስ ወይም ያለ ምክንያት የድካም ስሜት ሲሰማ
- ማቅለሽለሽ ወይም ማስታወክ
  አንዳንድ ሰዎች የINH ኪኒን መዉሰድ ሲጀምሩ የማቅለሽለሽ ስሜት ያድርባቸዋል። ይህ ከተሰማዎት ከኪኒንዎ ጋር መጠኑ አነስ ያለ ምግብ ለመብላት ይሞክሩ። ወይም ኪኒኑን ከመኝታ በፊት ይዉሰዱት። **የማቅለሽለሽ ስሜቱ ከሦስት ቀን በላይ ከቆየ ክሊኒክዎ ጋር ወዲያዉ ይደዉሉ።**
- የሆድ ሕመም
- ጠቆር ያለ ሽንት (የሻይ ወይም የቡና ቀለም)
- ቢጫ ቆዳ ወይም ዓይን
- የቆዳ ሽፍታ ወይም ማሳከክ
- እጅ ወይም እግር ላይ የመደንዘዝ ወይም የመነዝነዝ ስሜት
- ከሦስት ሳምንት በላይ የሚቆይ ሳል
- ማታ ማታ ላብ

**ከነዚህ ችግሮች ዉስጥ አንዱ ካልዎት ክሊኒክዎ ጋር ወዲያዉ ይደዉሉ - እስከሚቀጥለዉ ቀጠሮዎ ድረስ አይጠብቁ።**

**ሌሎች አስፈላጊ ነጥቦች:**

- INH በሚወስዱበት ጊዜ አልኮል መጠጣት ጉበትዎን ሊጎዳዉ ይችላል። የድብቅ ነቀርሳ ሕክምናዎን እስከሚጨርሱ ድረስ ቢራ፣ ወይን ወይም ሌላ አልኮል መጠጥ አይጠጡ።

- **ሌላ ዓይነት መድሃኒት እየወሰዱ ከሆነ ወይም ነፍሰ ጡር ከሆኑ ለዶክተርዎ ወዲያዉ ያስታዉቁ።**

# የድብቅ ነቀርሳ በሽታ ሕክምና - ገጽ 2

## መድሃኒቱን ባልወሰድ ምን ይሆናል?

INH ባይወስዱ ወይም ኪኒኑን ሳይጨርሱ ቶሎ ቢያቆሙ የንቁ ነቀርሳ በሽታ ሊነሳብዎት ይችላል። ይህ ማንኛውም ድብቅ ነቀርሳ ያለው ሰው ላይ በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት ይችላል። ይህ እርስዎ ላይ ወይም ቤተሰብዎ ላይ እስከሚደርስ አይጠብቁ!

## የ ቢሲጂ ክትባት ካለኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

የነቀርሳ በሽታ በተለመደባቸው አገሮች ውስጥ ብዙ ሰዎች ቢሲጂ የሚባል ክትባት ወስደዋል።  ቢሲጂ ልጆችን ከነቀርሳ መከላከል ቢችልም ለተወሰነ ዓመታት ብቻ ነው የሚቆየው።

ቢሲጂ የተከተቡ ሰዎች ነቀርሳ ሊይዛቸው ይችላል! ቢሲጂ ወስደው ከሆነ የድብቅ ነቀርሳ መድሃኒት በመውሰድ ራስዎን መከላከል ይችላሉ።

## ለኪኒኖቹ መክፈያ ገንዘብ ባይኖረኝስ?

ዶክተርዎን ወይም ነርስዎን ነፃ የነቀርሳ መድሃኒት እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይጠይቁ።

## ቤት/ቦታ ለቅቄ ወደ ሌላ ቤት/ቦታ ብሄድስ?

ወደ ሌላ ስቴት ወይም ከተማ ከለቀቁ ሕክምና የሚያገኙበትን ቦታ ከመሄድዎ አስቀድመው ይንገርዋቸው።  የነቀርሳ መድሃኒትዎ ከለቀቁም በኋላ እንደሚደርስዎ ማረጋገጥ ይችላሉ።

**እራስዎን፣ ቤተሰብዎንና ጓደኞችዎን ከነቀርሳ ይከላከሉ - የነቀርሳ መድሃኒትዎን በሙሉ ይውሰዱ!**

## የነቀርሳ መድሃኒቴን እንደወሰድ እንዴት ማስታወስ እችላለሁ?

የነቀርሳ መድሃኒትዎን በየቀኑ መውሰድ አለብዎት። ሳይወስዱ ብዙ ቀኖች ካሳለፉ መድሃኒቱ ላይሠራ ይችላል።  ዶክተርዎ ማቆም ይችላሉ እስከሚሉዎት ድረስ መውሰድዎን ይቀጥሉ።

ለማስታወስ ሊረዳዎት የሚችሉ አንዳንድ መንገዶች፥

- ኪኒኖችዎን በየቀኑ ፊት ለፊት ሊያይዋቸው የሚችሉት ቦታ ላይ ያስቀምጧቸው
- ቤተሰብ ወይም ጓደኛ በየቀኑ እንዲያስታውሶት ይጠይቁ
- ካሌንደርዎ ላይ መድሃኒት በወሰዱ ቁጥር በየቀኑ ምልክት ያድርጉ
- የኪኒን ማስታወሻ ሳጥን ይጠቀሙ
- ኪኒንዎትን ሲወስዱ በየቀኑ አንድ ዓይነት ሰዓት ላይ ይውሰዱ።  ለምሳሌ ጥርስዎን ከተቦረሹ በኋላ፣ ቁርስ ከበሉ በኋላ ወይም ልክ ከመተኛትዎ በፊት.

ሳይወስዱ የረሱት ቀኖች ካሉ ይጻፏቸውና በሚቀጥለው ጊዜ ዶክተርዎን ወይም ነርስዎን ይንገሯቸው።

**ዶክተርዎ/ክሊኒክዎ/ነርስዎ:**

______________________________

______________________________

______________________________

**ስልክ ቁጥር:** __________________________

Tuberculosis Prevention and Control Program
P.O. Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-5414
1-877-676-5414
www.health.state.mn.us/tb